# ስሙን ተገበረ  አሥራት አመረረ!

ለእጀ ሽካራውም ለእግረ ሰንጣቃ
ራስህን ሰጥተህ ሆነኸው ጠበቃ

አንት!  ያንጠረኛ ወገን የመንገድ አዳሪ
አንት! ለፍትህ ተሚጋች ቃል ኪዳን አክባሪ

የጫካው አንበሳ የከተማው ነብር
መልክህን ሳታበላሽ ቁንጅናህን ከምድር

ስሙን ተገበረ አሥራት አመረረ!

ደከመኝ ከማይሉት የዘለዓለም ጉዞ
ዕውነቱን ጠብቆ ቃል ኪዳኑን ይዞ

መዋጥ ቢቸግርም ልክ እንደ መተሬ
ሄዶብሻል አሥራት እሪ በይ ሀገሬ

ጓድህ ዓሊ ሁሴን

## ከቤተሰቦቹ መልዕክት

አስራት ለብዙ ወራት ታሞ ሳለ ላስታመማችሁት፣ በዚህ ቀውጢ
ጊዜ ለኛ ለቤተሰቦቹ ሙሉ ድጋፍ ለሰጣችሁን ሁሉ
የከበረ ምስጋና እናቀርባለን።

ባለቤቱ ወ/ሮ ታደለች ጉተማ ልጁ ወ/ት መሪ አፋን

**BENTA’S Funeral Home ,Inc**
630 St. Nicholas Ave.
New York, NY 10030
212-281-8850

# In Loving Memory



## አሥራት አፋን
## (አሥራት ፋንታዬ ገብረ መድኅን)

**ጥቅምት 1 ቀን 1941 - መጋቢት 1 ቀን 2005**

**170 S. Portland Ave**

**APT# 15H**

**Brooklyn NY 11217**

# የአሥራት አጭር የሕይወት ታሪክ

አሥራት ባደረበት ህመም ምክንያት ሲታከም ቆይቶ ባለፈው እሁድ መጋቢት 1 ቀን 2005 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶናል። አሥራት ከእናቱ ከወ/ሮ ካሰች አየለና ከአባቱ አቶ ፋንታዬ ገብረ መድኅን እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ጥቅምት 21 ቀን 1941 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ተወለደ። ዕድገቱ በአዲስ አበባ አዲስ ከተማ (መርካቶ) ከእናቱ ጋር ሆኖ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በአዲስ አባባ አርበኞች ትምህርት ቤት ፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አዲስ ከተማ በሚገኘው የልዑል መኮንን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናቋል።

አሥራት በሥራው ዓለም አዲስ አበባ ባንክ ይሠራ የነበረና የባንኩን የሠራተኞች ማህበር ከመሠረቱት አንዱ ነበር። ማህበሩ በሕግ ከታወቀም በኋላ የአዲስ አበባ ባንክ የሠራተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት እንዲሆን ተመርጦ ለመጀመሪያ ጊዜ የባንኩን ሠራተኞች መብት ያስጠበቀውን የጋራ ድርድር በማድረግ የጋራ ስምምነት ከባንኩ ሥራ አስኪያጆች ጋር በመፈራረም የሠራተኞች መብት አስጠባቂነቱን በተግባር በወጣትነት ዕድሜው ያስመሰከረ ቆራጥ ተጋይ ነበር። የየካቲት 1966 ዓብዮት ሲፈነዳም አሥራት የሠራተኞችን መብት በመደፍጠጥ በነፃ የመደራጀትን መብት የነፈገውን የደርግ ፋሺሺታዊ መንግሥት ከኢሠአማ የትግል ጓዶቹ ጋር በመሆን አጥብቆ በመታገሉ በቀንደኝነት በቀይ ሽብር ሊመታ ይፈለግ የነበር ጀግና ነበር።

ከ1969 ዓ.ም. በኋላም ወደ ገጠር (ትግራይ አሲምባ) የኢሕአፓን ጦር ኢሕአሠን በመቀላቀል ሲታገል ከፉኛ ቆስሎ ወደ ሱዳን ለህክምና እስከወጣበት ጊዜ ድረስ በገጠር ከደርግና ከዘረኞች ጋር ተፋልሟል። በ1980ቹ ከሱዳን ወደ አሜሪካ በስደተኝነት ከመጣ በኋላ በብሉ ክሮስ ብሉ ሺልድ ኢንሹራንስ ኩባንያና በፎርድሃም ዩኒቨርሲቲ እየሰራ ከሚወዳት የትዳር ጓደኛው ወ/ሮ ታደለች ጉተማና ከልጁ መሪ ኣፋን ጋር በኒውዮርክ ብሩክሊን ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለያቸው ድሪስ ኖሯል። አሥራት እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በኢሕአፓ አባልነት በጽናት የታገለ ጓድ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ሀገሩን ወዳድ፣ ሁሉን እንደጠባዩ የሚያቀርብና የሚያከብር ተወዳጅ ወንድም ነበር።

# የአሥራት የቀብር ሥነ ሥርዓት ፕሮግራም

## ፍታትና ስንብት

9:00 – 11:00

**ፍትሃተ ጸሎት** . . . . . . . . . . . . . . . . . *መሪ ጌታ ብርሃኑ ውድነህ*
*መልአከ ሠላም ካሳሁን ዳኛቸው*

**የስንብት መልዕክት ላላቸሁ** (ሁለት ሁለት ደቂቃዎች ብቻ)

**የአሥራት የሕይወት ታሪክ ይነበባል**

**የመጨረሻ የስንብት መልዕክት ከልጁ** . . . . . . . . . . . *ወ/ት መሪ አፋን*

የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ከቀኑ 1:00 ሰዓት ላይ
በሚከተለው አድራሻ ይፈጸማል

Forest Green Park Cemetery
535 Texas rd Morganville NJ 07751
Tel# 732-591-1501